# ብሄራዊ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበራት ስፖርት ፌዴሬሽን
# National Ethiopian Community Associations Sports Federation

## መተዳደሪያ ደንብ
## Constitution

## ክፍል አንድ

### አንቀጽ አንድ

1. መግቢያ

1.1 በአውስትራሊያ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበራት ስፖርት ፌዴሬሽን ከአውስትራሊያ የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማኅበር ካውንስል ጋር በመተባበር እና በመደጋገፍ በአውስትራሊያ የኢትዮጵያውያንን የስፖርት ተሳትፎና እንቅስቃሴ ለማጎልበትና ለማቀናጀት ማእከላዊ አመራርም ለመስጠት ከየክልሉ (States) በተወከሉ የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማኅበራት እና የስፖርት ተጠሪዎች፣ አሰልጣኞችና አባላት የተመሰረተ ፌዴሬሽን ነው። ፌዴሬሽኑ የትርፍ ድርጅት አይደለም። ፌዴሬሽኑ ከማንኛውም ዓይነት የፖለቲካ፣ የኃይማኖት የቋንቋ የዘር ተጽዕኖና ወገናዊነት ነጻ ነው።

### አንቀጽ ሁለት

2. ምሥረታ

2.1 ፌዴሬሽኑ በዚህ ህገ ደንብ (Constitution) በሰፈሩት ዓላማዎችና ድንጋጌዎች ላይ ተመሥርቷል።

2.2 የፌዴሬሽኑ መጠሪያ/መታወቂያ ስም ''ብሄራዊ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበራት ስፖርት ፌዴሬሽን'' የሚል ነው።

### አንቀጽ ሦስት

3. ትርጉም

* ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠው ድረስ በዚህ ህገ ደንብ መሠረት
3.1 '' የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማኅበራት'' ማለት በተለያዩ ክልሎች (States) የተደራጀና ህጋዊ ዕውቅናን ያገኙ (Incorporated) የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማኅበራት ማለት ነው::

3.2 ''የስፖርት ፌዴሬሽን'' ማለት በክፍል አንድ አንቀጽ አንድ ንዑስ አንቀጽ 1.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በክፍል አንድ አንቀጽ ሦስት 3.1 መሠረት ህብረት በመፍጠር በአንድ ፌዴሬሽን ስር የተዋቀሩት የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማኅበራት የስፖርት አካላት ኅብረት ማለት ነው።

3.3 "አባል" ማለት በዚህ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተዋቀሩትና ፌዴሬሽኑን የመሰረቱት የየክልሉ (States) የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማኅበራት የስፖርት አካላትና የፌዴሬሽኑን መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ በአባልነት የተመዘገበ ቡድን ወይም ድርጅት ወይም ግለሰብ ማለት ነው።

3.4 "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት በፌዴሬሽኑ ህገ ደንብ (Constitution) መሠረት የተዋቀሩና የፌዴሬሽኑ አባል የሆነ ሁሉ በአንድ የተወሰነ ስፍራና ጊዜ የሚገኙበት አጠቃላይ አውስትራሊያ አቀፍ ስብሰባ ማለት ነው።

3.5 "የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ" ማለት በጠቅላላ ጉባኤ ፌዴሬሽኑን ለተወሰነ ዓመት/ዓመታት ለመምራት የሥራ ሃላፊነት የተሰጠው ኮሚቴ ማለት ነው።

3.6 "ኮረም" ማለት ከፌዴሬሽኑ አባላት ቢያንስ ከ 51% የተገኙበት እንደ ምልዓተ ጉባኤ ተቆጥሮ የሚካሄድ ስብሰባ ማለት ነው።

3.7 "ህግ" ማለት ፌዴሬሽኑ የሚተዳደርበት ህገ ደንብ ማለት ነው።

## አንቀጽ አራት

4 መለያ አርማ እና ማህተም

4.1 ብሄራዊ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ማህበራት ስፖርት ፌዴሬሽን የራሱ የሆነ መለያ አርማ እና ማኅተም አለው።

## አንቀጽ አምስት

5. አድራሻ

5.1 የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ለፌዴሬሽኑ በተመረጠው ፕሬዚዳንት አባል ማኅበር ክልል (State) አድራሻ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

## አንቀጽ ስድስት

6. ዓላማ
ብሄራዊ የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማህበራት ስፖርት ፌዴሬሽን የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት።

6.1 በመላው አውስትራሊያ ክልል የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የስፖርት ዘርፎች ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማደራጀት ሁኔታዎችንም ማመቻቸት

6.2 በየክልሉ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስፖርተኞች ዓመታዊ የስፖርት ውድድር የሚያካሂዱበትን ማዕከላዊ ፕሮግራም ማዘጋጀትና ተግባራዊነቱንም መከታተል

6.3 በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.2 የተጠቀሰውን ዓመታዊ የስፖርት ውድድር በዓልን በሁሉም የአውስትራሊያ ክልሎች (States) ውስጥ በየተራ የሚደረግበትን ዕቅድ ማውጣትና ማስፈጸም

6.4 በየክልሉ ጠንካራ የስፖርት ኮሚቴዎችና ንዑሳን ኮሚቴዎች እንዲዋቀሩ እና ስፖርተኞችን እንዲያሰባስቡ መንገድ መፈላለግና በአስፈላጊው ሁሉ እገዛ ማድረግ። (የሕጻናት፣ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የአረጋውያን ስፖርታዊ እንቅስቃሴያችን በየክልሉ ማደራጀት)

6.5 ተተኪው ወጣት ትውልድ በአእምሮው ንቁ በአካልም ብቁ የሆነ ጤናማ አምራች ዜጋ እንዲሆን በስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚሰለጥንበትንና የሚሳተፍበትን ክልላዊና ፌደራላዊ መንገድ ማመቻቸት። በአስፈላጊው ሁሉ ማገዝ።

6.6 ተመሳሳይ ስፖርታዊ አደረጃጀትና እንቅስቃሴ ካላቸው የሌሎች ኮሚኒቲ ማኅበራት የስፖርት አካላት ጋር ግንኙነቶችን መፍጠር የስፖርት ውድድሮችን ማዘጋጀት።

6.7 ከኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማኅበራት ካውንስልና ከየክልሉ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ማኅበራት ጋር በመተባበር ለኢትዮጵያውያን ህብረትና ዕድገት አብሮ መስራት።

6.8 ለኢትዮጵያውያን በሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ክንውኖችና ዕቅዶች እና ዝግጅቶች ላይ (የባሕል፣ የአርት፣ ኢግዚቢሽኖች ወዘተ...) በመሳተፍ አስተዋጻኦ ማድረግ

6.9 ለፌዴሬሽኑ እድገትና ጥንካሬ ይጠቅማሉ ከሚባሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር።

6.10 ፌዴሬሽኑን ከሌሎች ሀገሮች (ምሳሌ ኒውዝላድ ወዘተ...) የኢትዮጵያውያን ስፖርት ተቋማት ጋር ማስተዋወቅ፣ የልምድ ልውውጥ ማድረግና ስፖርታዊ ውድድሮች የሚካሄዱበትን ሁኔታ መፍጠር

## ክፍል ሦስት

### አንቀጽ ሰባት

7. አባልነት

7.1 በየክልሉ (States) በኢትዮጵያውያን ማኅበርሰብ ማኅበራት የተደራጀ የስፖርት ቡድን እና ዘርፍ የዚህ ፌዴሬሽን አባል መሆን ይችላል።

7.2 በየክልሉ (States) ከኢትዮጵያውያን ማኅበርሰብ ማኅበራት ውጭ የተደራጀ የስፖርት ቡድን የፌዴሬሽኑን ህገ ደንብ (Constitution) ከተቀበለ አባል መሆን ይችላል።

7.3 በየትኛውም ክልል (States) የሚኖር ኢትዮጵያዊ ግለሰብ/አውስትራሊያዊ ዜጋ የፌዴሬሽኑን ህገ ደንብ (Constitution) ከተቀበለ አባል መሆን ይችላል።

7.4 በክፍል አንድ አንቀጽ አንድ 1.1 የተዘረዘረው እንደተጠበቀው ሆኖ በኢትዮጵያ መልክአ ምድር ከሚገኙት ጎሳዎች / ብሔር ብሄረሰቦች አንዱን ወይም የተወሰኑትን ወክሎ የተመሰረተ የስፖርት ቡድን ለጤናማ ስፖርታዊ ውድድር አደገኛ በመሆኑ የዚህ ፌዴሬሽን አባል መሆን አይችልም።

7.5 ማንኛውም ጸረ-ስፖርት አቋም ያለው ግለሰብም ሆነ ድርጅት የዚህ ፌዴሬሽን አባል መሆን አይችልም።

## አንቀጽ ስምንት

8. የአባልነት መብት

8.1 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል ሀሳቡን ያለአንዳች ገደብ በነጻ የመግለጽ መብት አለው

8.2 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት አለው

8.3 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አካል ከፌዴሬሽኑ አባልነት የመልቀቅ መብት አለው

8.4 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል የፌዴሬሽኑን መዛግብትና ሰነዶች የማየትና የመመርመር መብት አለው።

## አንቀጽ ዘጠኝ

9. የአባልነት ግዴታ

9.1 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል ለፌዴሬሽኑ ህገ ደንብ (Constitution) እና ለጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔዎች ተገዢ የመሆን ግዴታ አለበት

9.2 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል በፌዴሬሽኑ የሚወሰንበትን መዋጮ በወቅቱ የመክፈል ግዴታ አለበት።

9.3 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል ከፌዴሬሽኑ የተቀበለውን የሥራ ኃላፊነት የመወጣት ግዴታ አለበት።

9.4 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል ከፌዴሬሽኑ የተረከበውን ንብረት የመመለስ ግዴታ አለበት

9.5 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል ፌዴሬሽኑ በሚጠራው ስብሰባ የመገኘት ግዴታ አለበት

## አንቀጽ አስር

10. ከአባልነት ስለመወገድ

10.1 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል የፌዴሬሽኑን ህገ ደንብ (Constitution) እና ዓላማ የሚጻረር ተግባር ሲፈጽም ከተገኘ ከአባልነት ይወገዳል ይህም በስራ አስፈጻሚው የድምጽ ብልጫ ይወሰናል። ግለሰቡ እስከ ምልአተ ጉባኤው አቤቱታ ማቅረብ ይችላል

10.2 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል የፌዴሬሽኑን ንብረት ፋይናንስ ለግል ጥቅሙ ሲያውል ከተገኘ ከአባልነት ይወገዳል

10.3 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል ፌዴሬሽኑ በሚጠራው ጉባኤ ላይ ያለበቂ ምክንያት ለሦስት ተከታታይ ጊዜ ካልተገኘ ከአባልነት ይወገዳል

# ክፍል አራት

## አንቀጽ አስራ አንድ

11. የፌዴሬሽኑ አወቃቀር

ፌዴሬሽኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አደረጃጀቶች አሉት

11.1 ጠቅላላ ጉባኤ

11.2 የሥራ አመራር አካል

11.3 የኦዲት ኮሚቴ

11.3 የመማክርት ሸንጎ

## አንቀጽ አስራ ሁለት

12. የጠቅላላ ጉባኤ ጥንቅርና መደበኛ ስብሰባ

12.1 ጠቅላላ ጉባኤው ከየክልሉ (States) የፌዴሬሽኑ አባላት ተወካዮች የሚገኙበት ጉባኤ ነው።

12.2 በንዑስ አንቀጽ 12.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የጉባኤውን ውክልና የሚወስዱት ክልሎች (States) እና መጠን

ሀ. ቪክቶሪያ -----አምስት ወኪሎች
ለ. ኒው ሳውዝ ዌልስ---------አምስት ወኪሎች
ሐ. ሳውዝ አውስትራልያ----አምስት ወኪሎች
መ. ምዕራብ አውስትራሊያ-----አምስት ወኪሎች
ሠ. ክዊንስላንድ-----------ሦስት ወኪሎች
ረ. ታዝማኒያ ------------ ሦስት ወኪሎች
ሸ. ኖርዘን ቴሪቶሪ --------- አንድ ወኪል
ቀ. አውስትራሊያ ካፒታል ቴሪተሪ -------- ሁለት ወኪሎች

12.3 ጠቅላላ ጉባኤው በንዑስ አንቀጽ 12.2 መሰረት 29 ተወካዮች ይኖሩታል

## አንቀጽ አስራ ሦስት

13. የጠቅላላው ጉባኤ መደበኛ ስብሰባና ኮረም

13.1 ጠቅላላ ጉባኤው በዓመት አንዴ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል

13.2 የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ከዲሴምበር 26 እስከ ዲሴምበር 30 ባሉት ዓመታዊ የስፖርት ውድድር ቀናት ውስጥ ይካሄዳል።

13.3 የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ኮረም እንደተሟላ የሚቆጠረው

ሀ. በአንቀጽ አስራ ሁለት ንዑስ አንቀጽ 12.3 ከተጠቀሱት የጠቅላላ ጉባኤው ተወካዮች መካከል በቁጥር አስራ ሰባት ወኪሎች ሲገኙ ወይም

ለ. በአንቀጽ አስራ ሁለት ንዑስ አንቀጽ 12.2 መሰረት የአራት ክልሎች (States) ወኪሎች ከተገኙ ይሆናል።

13.4 ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ የሚቀርቡት አጀንዳዎች ጉባኤው ከመካሄዱ ስምንት

ሳምንት (ሁለት ወራት) በፊት ለየክልሉ (States) የፌዴሬሽኑ አባላት በጽሁፍ መድረስ አለባቸው።

13.5 ጠቅላላ ጉባኤው በመደበኛ ስብሰባው ላይ ከቀረቡት አጀንዳዎች ውጭ አይወያይም።

13.6 በንዑስ አንቀጽ 13.5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከጉባኤው ተወካዮች አስቸኳይ የመነጋገሪያ አጀንዳ ከቀረበና ከጉባኤው ተሳታፊዎች ሁለት ሦስተኛው በድምጽ ከደገፈው በተጨማሪ አጀንዳነት ተይዞ ውይይት ይደረግበታል።

13.7 በጠቅላላው ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ ላይ የሚተላለፉት ውሳኔዎች የመጨረሻ ውሳኔዎች ናቸው። የመደበኛ ስብሰባ ውይይቶችና ውሳኔዎች ሁሉ በቃለ ጉባኤ ይያዛሉ።

## አንቀጽ አስራ አራት

14. የጠቅላላው ጉባኤው ስልጣንና ኀላፊነት

14.1 የጠቅላላ ጉባኤው የፌዴሬሽኑን የስራ አስኪያጅ አካላት ይመርጣል፣ ከስልጣን ያስወግዳል፣ በጎደለ አመራር አካል ቦታ ይተካል።

14.2 ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የሚቀርቡትን ዓመታዊ የሥራ ሪፖርቶች ያዳምጣል፣ ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሰጣል።

14.3 የፌዴሬሽኑን የፋይናንስና ኦዲት ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሰጣል

14.4 በቀረቡት አጀንዳዎች ላይ ይወያያል፣ ውሳኔ ያስተላልፋል።

14.5 የፌዴሬሽኑን ፕሮጀክትና በጀት ይመረምራል ውሳኔ ያስተላልፋል

14.6 የፌዴሬሽኑ ዓመታዊ የስፖርት ውድድር በተስተካከለ ሁኔታና ስፖርታዊ ጨዋነት መካሄዱን ይቆጣጠራል።

14.7 የፌዴሬሽኑ ዓመታዊ የስፖርት ውድድር የሚካሄድበትን ክልል (States) ይወስናል።

14.8 ዓመታዊ የስፖርት ውድድሩን ለሚያኪያሂደው ክልል (States) በጀት ይመድባል። የሰው ኃይልና የማቴሪያል እገዛ ያደርጋል።

14.9 በጠቅላላ ጉባኤው ላይ የሚተላለፍ ውሳኔ ሁሉ በድምጽ ብልጫ ይሆናል።

14.10 በንዑስ አንቀጽ 14.9 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በድምጽ አሰጣጥ ጉባኤው እኩል ከተከፈለ የጉባኤው ሰብሳቢ ድምጽ የሚደግፈው ውሳኔ ያልፋል።

14.11 በአንቀጽ አስር ከንዑስ አንቀጽ 10.1 እስከ 10.3 የተዘረዘሩት ከፌዴሬሽኑ አባልነት የማስወገድ ኃላፊነት የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ይሆናል።

14.12 የፌዴሬሽኑን መተዳደሪያ ደንብና የውስጥ ህግጋት የማሻሻልም ሆነ የመሰረዝ መብት የጠቅላላው ጉባኤው ነው።

14.13 ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ኃላፊነትና ሥልጣኑ የጠቅላላው ጉባኤ ብቻ ነው።

14.14 በንዑስ አንቀጽ 14.13 ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የሚቀርበው አጀንዳ ለውይይት የሚቀርበው ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ማኅበራት ውስጥ ሦስት አራተኛው ከደገፉት ብቻ ይሆናል።

14.15 ጠቅላል ጉባኤው የፌዴሬሽኑን የውስጥ መመሪያና ደንብ ያጸድቃል። ተፈጻሚነቱንም ያረጋግጣል።

## አንቀጽ አስራ አምስት

15. የጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ

15.1 ጠቅላላ ጉባኤው ከመደበኛ ዓመታዊ ስብሰባ ሌላ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

15.2 በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 15.1 የሚጠራው አስቸኳይ ስብሰባ በፌዴሬሽኑ ሥራ አመራር አካል ፕሬዝዳንት በኩል ነው።

15.3 አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚጠራውም
   ሀ. ለፌዴሬሽኑ ህልውና የሚያሰጋ አደገኛ ሁኔታ ሲፈጠር
   ለ. የተፈጠረውም አደጋ እስከ ጠቅላላው ጉባኤ መደበኛ የስብሰባ ወቅት ፋታ የማይሰጥ ሲሆን
   ሐ. በንዑስ አንቀጽ 15.3 በ ሀ. እና ለ ለተጠቀሱት ዝርዝር ሁኔታዎች ከፌዴሬሽኑ የየክልሉ (States) አባል ማኅበራት ተወካዮች መካከል 50% (ግማሽ) የሚሆኑት የፈረሙበት የአስቸኳይ ስብሰባ ጥሪ ዝርዝር ለፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ሲደርሰው ብቻ ፕሬዝዳንቱ አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ጥሪ ያደርጋል።

# ክፍል አምስት

## አንቀጽ አስራ ስድስት

16. የስራ አመራር አካላት ብዛትና የስራ ዘመን

16.1 ፌዴሬሽኑ ስምንት (8) የስራ አመራር አካላት አሉት።

16.2 የፌዴሬሽኑ የስራ አመራር አካላትም
   16.2.1. ፕሬዝዳንት
   16.2.2. ዋና ጸሀፊ
   16.2.3. ም/ጸሀፊ
   16.2.4. የበጀትና የሂሳብ ክፍል ኃላፊ
   16.2.5. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ
   16.2.6. የአጠቃላይ አገልግሎትና ንብረት ክፍል ኃላፊ
   16.2.7. የሥነ ስርአት (Discipline) ጉዳይ ኃላፊ
   16.2.8. የዓመታዊ ስፖርት ውድድር ዝግጅት አስተባባሪ ኃላፊ

16.3 የፌዴሬሽኑ የስራ አመራር አካላት የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ነው።

16.4 የፌዴሬሽኑ የስራ አመራር አካላት የሚመረጡት በጠቅላላው ጉባኤ በድምጽ ብልጫ ነው።

## አንቀጽ አስራ ሰባት

## 17. የስራ አመራር አካላት ስልጣንና ኃላፊነት

### 17.1 ፕሬዝዳንት

17.1.1 የፌዴሬሽኑን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በበላይነት ይቆጣጠራል፤ ይመራል።
17.1.2 የጠቅላላ ስብሰባውንም ሆነ የሥራ አመራር ኮሚቴውን ስብሰባ ይመራል።
17.1.3 ተጠሪነቱ ለፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል።
17.1.4 በስራ ላይ ያሉትን የስራ አመራር ኮሚቴ አባላትንና የሌሎቹን ተጨማሪ የኮሚቴ አባላትን እንደዚሁም የስራ ክፍሎቻቸውን ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤ ይመራል።
17.1.5 የፌዴሬሽኑ አባላት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያበረታታል፤ ያነቃቃል።
17.1.6 ውክልና በሚያስፈልግበት ስፍራ ሁሉ ፌዴሬሽኑን ይወክላል
17.1.7 በፌዴሬሽኑ ወጪ ሰነዶች ላይ ይፈርማል
17.1.8 የተቅላላ ጉባኤውን መነጋገሪያ አጀንዳ ከጸሐፊው ጋር በመተባበር እንዲዘጋጅ ያደርጋል

### 17.2 ዋና ፀሐፊ

17.2.1 ከፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ጋር በመመካከር የፌዴሬሽኑን ስራ ያከናውናል የፌዴሬሽኑን ጽ/ቤት ሥራ ይሰራል።
17.2.2 ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመመካከር የጠቅላላ ጉባኤውንና የስራ አመራር ኮሚቴውን መነጋገሪያ አጀንዳዎች ያዘጋጃል።
17.2.3 የጠቅላላ ጉባኤውንና የስራ አመራር ኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ በሪኮርድ ይይዛል
17.2.4 ከፌዴረሽኑ ወጪ የሚሆኑ ደብዳቤዎችን ያዘጋጃል
17.2.5 የፌዴሬሽኑን መተዳደሪያ ደንብ አባላት እንዲያውቁት ያደርጋል
17.2.6 የፌዴሬሽኑ አጠቃላይ ስብሰባ ሲጠራ አባላቱ ሁሉ እንዲያውቁት አስቀድሞ አስፈላጊውን ዝግጅትና ጥሪ ያደርጋል
17.2.7 የማኅበሩን ማህተም፣ የአባላት መዝገብና ሰነዶችን በሙሉ በአግባቡ ይይዛል
17.2.8 የሰባላትን ዝርዝር ይመዘግባል፤ ይይዛል
17.2.9 የፌዴሬሽኑ ለፕሬዝዳንት ሊገኝ በማይችልበት አጋጣሚ ፕሬዜዳንቱን ወክሎ ይሰራል

### 17.3 ምክትል ፀሀፊ

17.3.1 የፌዴሬሽኑ ምክትል ፀሃፊ የፌዴሬሽኑን ዋና ፀሃፊ በስፈላጊው ሁሉ ያግዛል
17.3.2 ዋና ፀሀፊው በማይገኝበት አጋጣሚ የዋና ፀሀፊውን ተግባር ያከናውናል

### 17.4 የበጀትና የሂሳብ ክፍል ኃላፊ

17.4.1 ከፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንትና ጸሐፊ ጋር በመመካከር ይሰራል
17.4.2 የማኅበሩን በጀትና ገንዘብ አያያዝ በተመለከተ ኃላፊ ይሆናል
17.4.3 የሂሳብ አሰራሩና መዝግብት በትክክልና በስጥጋቢ ሁኔታ መመዝገባቸውንና መያዛቸውን ያረጋግጣል
17.4.4 ማንኛውም ገንዘብ ነክ ዟሮችና ወጪዎች በህገ ደንቡ መሰረት መፈጸማቸውንና መመዝገባቸውን ያረጋግጣል
17.4.5 የፌዴሬሽኑን ካፒታል ለማሳደግም ሆነ ገቢ ለማስገኘት የሚያስችሉ የበጀት ጥያቄዎችን ለተለያዩ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ያቀርባል
17.4.6 ከአባላት የሚገቡ መደበኛ መዋጮዎች በወቅቱ ገቢ መሆናቸውን ያረጋግጣል

17.4.7 የዓመቱን የሁሳብ ሪፖርት መግለጫ ያዘጋጃል
17.4.8 የወጪና የገቢ ሰነዶችን በትክክል ይይዛል
17.4.9 ማንኛውንም የገንዘብ ገቢና ወጪ ሰነዶች፣ ቼኮች፣ የባንክ ድራፍቶች እና የመሳሰሉት በሁለት የኮሚቴ አባላት ተፈርመው ወጪ መሆናቸውን ያረጋግጣል
17.4.10 በበጀት ዓመት መዝጊያ ሂሳቡን በሂሳብ መርማሪዎች/ ኦዲተሮች ያስመረምራል
17.4.11 በፌዴሬሽኑ የሂሳብ ወጪ ሰነዶች ላይ ይፈርማል

17.5 የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ

17.5.1 ፌዴሬሽኑን በመወከል መሰል ዓላማና ግብ ካላቸው ድርጅቶች ከየክልሉ የኢትዮጵያውያን ማህበረ-ሰብ ማህበራት የስፖርት ተጠሪዎች ለፌዴሬሽኑ እድገት ይረዳሉ ተብሎ ከሚታመንባቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ከፌዴሬሽኑ ፕሬዝደንት ጋር በመመካከር ግንኙነት ይፈጥራል
17.5.2 በዓመታዊ የፌዴሬሽኑ የስፖርት በአል ላይ በአሉን በማስተባበርና አስፈላጊ የሆኑትን ግንኙነቶች በመጠቀም ለበአሉ ስኬታማነት ከሌሎች ጋር በመተባበር ይሰራል
17.5.3 የፌዴሬሽኑን መቀላቀል ለሚፈልጉ በፌዴሬሽኑ ህገ-ደንብ መሰረት መረጃ በመስጠት አባላትን ይመለምላል

17.6 የአጠቃላይ አገልግሎትና የንብረት ክፍል ኃላፊ

17.6.1 የፌዴሬሽኑን ማንኛውንም ቁሳዊ ተንቀሳቃሽ ንብረት ይመዘግባል፣ ይይዛል
17.6.2 ለፌዴሬሽኑ ይጠቅማሉ ተብለው የሚገዙ ንብረቶችን ደረሰኝና ሰነድ ያዘጋጃል፣ ይይዛል
17.6.3 አልቂ የሆኑ ማንኛቸውንም የፌዴሬሽኑን መገልገያዎች (ኳስ፣ መርብ ወዘተ...) በአዲስ መተካት ሲያስፈልጋቸውም ለፌዴሬሽኑ ስራ አመራር ኮሚቴ በማቅረብ እንዲገዙ ያደርጋል፣ በትክክል መያዛቸውንም ያረጋግጣል
17.6.4 በዓመታዊው የፌዴሬሽኑ የስፖርት በአል ወቅት ለስፖርቱ ማካሄጃ የሚያስፈልጉ ንብረቶችን (ኳስ፣ መርብ ወዘተ...) ከክልሉ የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴ ጋር በመነጋገር እንደ አስፈላጊነታቸው ግልጋሎት ላይ እንዲውሉ ያደርጋል። በዓሉ ሲጠናቀቅም በትክክል ተረክቦ ይይዛል

17.7 የሥነ-ሥርዓትና ዲሲፕሊን ጉዳይ ኃላፊ

17.7.1 በፌዴሬሽኑ ውስጥ በሥነ-ሥራዓትና ዲሲፕሊን ጉዳይ የሚከሰቱ ችግሮችን ሁሉ ይመረምራል ለፕሬዝዳንቱም ሪፖርት ያደርጋል
17.7.2 በዓመታዊ የፌዴሬሽኑ የስፖርት በዓል ውድድር ላይ ውድድሩ በስፖርትዊ ጨዋነትና እኩልነት መካሄዱን በቅርብ በመገኘት ይከታተላል
17.7.3 በዓመታዊው የፌዴሬሽኑ የስፖርት በዓል ወቅት ዳኝነት ያለ አድልዎ መፈጸሙን በቅርብ ይከታተላል
17.7.4 በዓመታዊው የፌዴሬሽኑ የስፖርት በዓል ውድድር ላይ ከአዘጋጁ ክልል ጋር በመሆን በአስፈላጊው ሁሉ ይተባበራል

17.8 የዓመታዊ የስፖርት ውድድር በዓል አስተባባሪ

17.8.1 የፌዴሬሽኑ ዓመታዊ የስፖርት በዓል ዝግጅትንና አፈጻጸምን በተመለከተ

ከአዘጋጁ ክልል ጋር በቅርብ በመመካከር ይሰራል፣ በአስፈላጊው ሁሉ ይተባበራል

17.8.2 የበዓሉን አዘገጃጀት ፕሮግራም፣ የተጨዋቾቹን ማረፊያና ለትራንስፖርት ለውውድድሩ ማካሄጃ አስፈላጊ ቁሳቁሶች (ኳስ፣ መረብ፣ ወዘተ...) በሚገባ መሟላታቸውን በቅርብ በመከታተል ለፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ውድድሩ ከመካሄዱ ሁለት ሳምንት በፊት የጽሁፍ ሪፖርት ያቀርባል

## አንቀጽ አስራ ስምንት

18.1 የኦዲት ኮሚቴ

- 18.1.1 የኦዲትና ሂሳብ ኮሚቴ በፌዴሬሽኑ ጠቅላላው ጉባኤ ሙያውና ችሎታው ካላቸው አባላት ይመረጣል።
- 18.1.2 የኦዲት ኮሚቴው ሶስት አባላት ይኖሩታል
- 18.1.3 የኦዲት ኮሚቴው የፌዴሬሽኑ ስራ አመራር ኮሚቴ የተመደበለትን የስራ ዘመን ከመፈጸሙና ለጠቅላላ ጉባኤ

19.1 የመማክርት ጉባኤ

- 19.1.1 የመማክርት ጉባኤ እንደ አስፈላጊነቱ በጠቅላል ጉባኤው ይሰየማል
- 19.1.2 የመማክርት ጉዳይ የሚሰየመው
  - ሀ. በፌዴሬሽኑ አባላት መካከል ችግር ሲፈጠርና ችግሩንም ለመፍታት ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አቅምና ችሎታ በላይ ሲሆን
  - ለ. የፌዴሬሽኑ ህልውና አደጋ ላይ ሲሆንና አደጋውን ለመከላከል የመማክርት ጉባኤን ማቋቋም ሲያስፈልግ
- 19.1.3 የመማክርት ጉባኤ የተመረጠበትን ተልዕኮ ሲጨርስ ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ካቀረበ በኋላ ከኃላፊነት ይወርዳል

# ክፍል ስምንት

## አንቀጽ ሃያ

20.1 የፌዴሬሽኑ የገቢ ምንጭ

- 20.1.1 የፌዴሬሽኑ የገቢ ምንጮች
  - ሀ. ከአባላት የሚገኝ የአባልነት መመዝገቢያ
  - ለ. በዓመቱ ከአባላት የሚገኝ የአባላት ክፍያ
  - ሐ. ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚገኝ እርዳታ
  - መ. ከተለያዩ ዝግጅቶች (ትኬት፣ ተምቦላ ወዘተ...) የሚገኝ ገቢ
  - ሠ. ከዓመታዊ የስፖርት ውድድር በዓል ዝግጅት ከወጪ ቀሪ ገቢ ሃያ ፐርሰንት (20%)
  - ረ. ከተለያዩ ስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶች

# ክፍል ዘጠኝ

## አንቀጽ ሃያ አንድ

21.1 ፌዴሬሽኑን ስለ ማፍረስ

21.1.1 ፌዴሬሽኑን የማፍረስ ኃላፊነትና ስልጣን የጠቅላላው ጉባኤው ብቻ ነው

21.1.2 ፌዴሬሽኑ የሚፈርሰው ከፌዴሬሽኑ አባላት ሰባ አምስት ፐርሰንት (75%) ከተስማሙና በጽሑፍና በፊርማቸው ካረጋገጡ ብቻ ይሆናል

# ክፍል አሥር

## አንቀጽ ሃያ ሁለት

22.1 የፌዴሬሽኑ ገንዘብና ንብረት

22.1.1 በአንቀጽ 21.1 በንዑስ አንቀጽ 21.1.1 እና 21.1.2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፌዴሬሽኑ ሲፈርስ የፌዴሬሽኑ ገንዘብና ንብረት ለፌዴሬሽኑ አባል ማኅበራት ወይም ለኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማኅበራት በእኩል ድርሻ እንዲዳረስ ይደረጋል

# ክፍል አሥራ አንድ

## አንቀጽ ሃያ ሶስት

23.1 ተጠያቂነት

23.1.1 ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል/ አባላት የስራ አመራር አካል/ አካላት የፌዴሬሽኑን ገንዘብና ንብረት ለግል ጥቅም ካዋለ/ ካዋሉ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል/ ይሆናሉ

# ክፍል አሥራ ሁለት

## አንቀጽ ሃያ አራት

24.1 ክፍያ

24.1.1 ፌዴሬሽኑን በስራ አመራርም ሆነ በሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች የሚያገለግሉ ተመራጮች ሁሉ ምንም አይነት ክፍያ አይኖራቸውም

# ክፍል አሥራ ሦስት

## አንቀጽ ሃያ አምስት

25.1 ማሻሻያ

25.1.1 ይህ መተዳደሪያ ደንብ በፌዴሬሽኑ አባላት ጠቅላላ ጉባኤ ስድሳ ፐርሰንት (60%) ከተደገፈ በከፊልም ሆነ በሙሉ ሊሻሻል ይችላል

# ክፍል አሥራ አራት

## አንቀጽ ሃያ ስድስት

26.1 ልዩ ልዩ

26.1.1 የፌዴሬሽኑ የስራ አመራር አካል በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተመስርቶ እንደ አስፈላጊነቱ የውስጥ መመሪያ ሕጎችንና የንዑስ ኮሚቴ የስራ ደንቦችን የማውጣትና ለጠቅላላ ጉባኤው የማቅረብ መብት አለው

# ክፍል አሥራ አምስት

## አንቀጽ ሃያ ሰባት

27.1 ተፈጻሚነት

27.1.1 ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከአፕሪል 1 (April 1, 2007) ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**ፓራማታ ኒው ሳዝ ዌልስ**
**PARRAMATTA, SYDNEY, NEW SOUTH WALES**
**APRIL 1, 2007.**